# የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን

## በእንስሳት ጤና ባለሙያ የሚታዘዙ እና ያለማዘዣ ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒት ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 1022/2016

ጳጉሜ፣ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ማውጫ

መግቢያ ............ Error! Bookmark not defined.

ክፍል አንድ ............ 2

ጠቅላላ ............ 2

1. አጭር ርዕስ ............ 2

2. ትርጓሜ ............ 2

3. የተፈፃሚነት ወሰን ............ 3

ክፍል ሁለት ............ 4

የእንስሳት መድኃኒትን ስለማዘዝ  እና ስለማደል ............ 4

4. የእንስሳት መድኃኒትን ስለማዘዝ ............ 4

6. በማዘዣ ወረቀት የታዘዘ መድኃኒት ስለማደል ............ 6

7. ቁጥጥር የሚደረግበት የእንስሳት መድኃኒት ስለማዘዝ ............ 6

8. በልዩ ማዘዣ የእንስሳት መድኃኒት ስለማደል ............ 7

9. የእንስሳት መድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ሕጋዊነት ............ 8

ክፍል ሦስት ............ 8

ያለማዘዣ ወረቀት መድኃኒትን ስለማደል ............ 8

10. ያለማዘዣ ወረቀት ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒቶች ............ 8

11. የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ ግዴታዎች ............ 9

12. የታካሚ እንስሳት ባለቤት ግዴታዎች እና ኃላፊነቶች ............ 10

14. መዝገብ አያያዝ ............ 12

15. አስተዳደራዊ እርምጃ ............ 13

16. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች ............ 13

17. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ ............ 13

## <u>በእንስሳት ጤና ባለሙያ የሚታዘዙ እና ያለማዘዣ ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒት ለመወሰን የወጣ መመሪያ</u>

በእንስሳት ሐኪም ብቻ የሚታዘዙ፣ በእንስሳት ጤና ባለሙያ የሚታዘዙ እና ያለእንስሳት ጤና ባለሙያ ትዕዛዝ የሚታደሉ መድኃኒት በመለየትና በመወሰን አጠቃቀማቸውን መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በእንስሳት ጤና ባለሙያ የሚታዘዙ የእንስሳት መድኃኒት ከባለሙያ ትዕዛዝ ውጭ በመጠቀም ሊከሰት ከሚችል የእንስሳት እና የህብረተሰብ ጤና ችግር መከላከል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የእንስሳት ጤና ባለሙያ ማዘዣ ወረቀት ሳያስፈልግ የእንስሳት መድኃኒት ጥቅም ላይ ለማዋል ህጋዊ አሰራር ማስቀመጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ባለስልጣኑ በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀጽ 28 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፤

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "**በእንስሳት ጤና ባለሙያ የሚታዘዙ እና ያለማዘዣ ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒት ለመወሰን የወጣ መመሪያ** ቁጥር 1022/2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

2. **ትርጓሜ**

በእንስሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን አዋጅ ቁጥር 728/2004 አንቀጽ 2 የተቀመጡ ትርጓሜዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. "**ያለማዘዣ ወረቀት የሚታደሉ የእንስሳት መድኃኒቶች**" ማለት ያለእንስሳት ጤና ባለሙያ የጽሁፍ ትዕዛዝ በታካሚው እንስሳት ባለቤት በቀጥታ ከሕጋዊ የእንስሳት መድኃኒት ቤት ሊገዙ የሚችሉ መድኃኒት ነው፤

2. "**በእንስሳት ጤና ባለሙያ የሚታዘዙ መድኃኒቶች**" ማለት በእንስሳት ጤና ባለሙያ በጽሁፍ ትዕዛዝ ብቻ ከእንስሳት መድኃኒት ቤት ተገዝቶ ለታካሚው እንስሳት በባለሙያ የሚታዘዝ መድኃኒት ነው፤
3. "**ማዘዝ**" ማለት የእንስሳት መድኃኒትን ለታካሚው እንስሳት እንዲገዛ ወይም እንዲያገኝ ለታካሚ እንስሳት ባለቤት በፅሁፍ የሚሰጥ ትዕዛዝ ነው፤
4. **"የእንስሳት መድኃኒት ማዘዣ ወረቀት"** ማለት በእንስሳት ጤና ባለሙያ ተጽፎና ተፈርሞ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ማዘዣ መሣሪያ አማካኝነት የሚሰጥ ትዕዛዝ ነው፤
5. **"የእንስሳት ጤና ባለሙያ"** ማለት ታካሚ እንስሳትን በመመርመር የበሽታውን ዓይነት የሚለይና የሚያክም የእንስሳት ሀኪም ወይም ሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎችን ያካትታል፤
6. **"ማደል"** ማለት የእንስሳት መድኃኒት ለታካሚ እንስሳት ባለቤት ስለመድኃኒቱ አጠቃቀም ከበቂ የቃል ወይም የጽሁፍ ምክር ጋር መድኃኒት መስጠት ነው፤
7. "**የእንስሳት ጤና ተቋም**" ማለት የእንስሳት ህክምና አገልግሎት የሚያከናውን ማንኛውም የመንግስት ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ወይም የግል ተቋም ነው፤
8. "**ቁጥጥር የሚደረግባቸው የእንስሳት መድኃኒቶች**" ማለት በተባበሩት መንግስታት ድርጅት በ2001 ዓ.ም አለም አቀፍ ስምምነት መሠረት ቁጥጥር እንዲደረግበት የተለየ የእንስሳት መድኃኒት ነው፤
9. **"ልዩ የእንስሳት መድኃኒት ማዘዣ ወረቀት"** ማለት ናርኮቲክ የእንስሳት መድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸው የእንስሳት መድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ወይም የሳይኮቲሮፒክ ንጥረ ነገር ማዘዣ ወረቀት ማለት ነው፤
10. **"የታካሚ እንስሳት ባለቤት"** ማለት ታካሚ እንስሳትን የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ወደ እንስሳት ጤና ተቋም የሚወስድ እና ከእንስሳት መድኃኒት ቤት ለታካሚ እንስሳት መድኃኒት የሚገዛ ማንኛውም ሰው ነው፤
11. **"ባለስልጣን"** ማለት የኢትዮጵያ ግብርና ባለስልጣን ነው፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የእንስሳት መድኃኒትን በሚያዙ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች ወይም የእንስሳት መድኃኒትን በሚያድሉ የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያዎች እና በእንስሳት መድኃኒት ቤት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የእንስሳት መድኃኒትን ስለማዘዝ  እና ስለማደል

## 4. የእንስሳት መድኃኒትን ስለማዘዝ

1. በእንስሳት ጤና ባለሙያ የሚታዘዙ መድኃኒት በዚህ መመሪያ ዕዝል 5 መሠረት ደረጃውን በጠበቀ ማዘዣ ወረቀት ብቻ መታዘዝ አለበት፤
2. በዚህ መመሪያ አባሪ በሆነው ዕዝል 2 ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ ጥብቅ ቁጥጥር የሚያስፈልጋቸው ሙሉ የእንስሳቱን አካል የሚያደነዝዙ ወይም አዳዲስ የመድኃኒት ንጥረ ነገሮች የያዙ ወይም ሆርሞኖች ወይም አናልጀቲክና ሴዳቲቭ የእንስሳት መድኃኒት ማዘዝ የሚችለው የእንስሳት ሐኪም ብቻ ነው፤
3. በዚህ መመሪያ አባሪ በሆነው ዕዝል 3 ዝርዝር ውስጥ የተካተቱ የእንስሳት መድኃኒት በእንስሳት ጤና ባለሙያ መታዘዝ አለበት፤
4. ሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች በእንስሳት ሐኪም ቁጥጥር ስር ካልሆነ በስተቀር በእንስሳት ሐኪም ትዕዛዝ ብቻ የሚሰጡ መድኃኒት እንዲያዙ አይፈቀድላቸውም፤
5. ማንኛውም የእንስሳት ጤና ባለሙያ የእንስሳት መድኃኒት በሚያዝበት ጊዜ የመድኃኒቱን የፅንስ ስም መጠቀም አለበት፤
6. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ለትክክለኛው ታካሚ እንስሳት እንዲሰጥ በእንስሳት ጤና ባለሙያ ከታዘዘ ተመላሽ መሆን አይችልም፤
7. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ መድኃኒቱ የታዘዘው ለትክክለኛው ታካሚ እንስሳት ወይም ዶዝ ወይም አወሳሰድ ወይም ጊዜ ወይም ድግግሞሽ ካልሆነ ያዘዘውን ባለሙያ በማማከር እንደገና ሊታዘዝ ወይም ተመላሽ ሊደረግ ይችላል፤

8. የእንስሳት መድኃኒት ጎጂ ባህሪያት ወይም ያልተሳካ የሕክምና ክስተት በሚፈጠርበት ጊዜ የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች መከታተል አለበት፤

9. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ቤት በእንስሳት ጤና ባለሙያ ትዕዛዝ ብቻ የሚሰጥ መድኃኒት በህገ-ወጥ ማዘዣ ወረቀት መሰጠቱን ካወቀ በአካባቢው ለሚገኝ የእንስሳት ጤና ተቋም ወይም ግብርና ቢሮዎ ማሳወቅ አለበት፤

10. በዚህ መመሪያ ዕዝል 3 የተዘረዘረው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉትን መመዘኛ የሚያሟላ የእንስሳት መድኃኒት በእንስሳት ጤና ባለሙያ ትዕዛዝ ብቻ መሰጠት አለበት፡-

   ሀ) ጥቅም ላይ በሚውልበትም ጊዜ ቢሆን አደጋን የመፍጥር ዕድሉ ሰፊ የሆነ፣

   ለ) በተደጋጋሚ እና በስፋት ያለአግባብ ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ፣

   ሐ) ተጨማሪ ምርመራ የሚሹ ንጥረ ነገሮችን በውስጡ የያዘ ከሆነ፣

   መ) ከአምራች ፋብሪካ ገላጭ ጽሁፍ ውጪ የሚታዘዝ ከሆነ፣

   ሠ) በእንስሳት ጤና ባለሙያ አዘውትሮ ክትትል የሚያስፈልገው ወይም ያለአግባብ ለመጠቀም ወይም ላልተፈለገ ዓላማ ላይ የመዋል ሥጋት ያለው ከሆነ፣

   ረ) አዳዲስ ኬሚካል ወይም ንጥረ ነገር ካለው፣

   ሰ) የተህዋስያን መላመድ በስፋት እንደሚፈጠርበት ስጋት የሚፈጥር ከሆነ፣

   ሸ) አንቲዲፕረሳንት ወይም አንቲሳይኮቲክ ወይም አንዥላይት ንጥረ ነገር ከያዘ፣

   ቀ) የውጪ ጥገኛ መድኃኒት ከሆነ፣

   በ) ኤሌክትሮላይት፣

   ተ) ለመመረዝ የሚያገለግል መድኃኒት፣

   ቸ) በመርፌ መልክ የሚሰጥ መድኃኒት፡፡

5. **የተከለከሉ ተግባራት**

   1. ከእንስሳት ጤና ባለሙያ ውጪ ባልተፈቀደለት ሰው የእንስሳት መድኃኒት ማዘዝ ፈፅሞ የተከለከለ ተግባር ነው፤

   2. የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች መድኃኒት በሚያዙበት ጊዜ በንግድ ስም መጠቀም የለባቸውም፤

   3. ከእንስሳት ጤና ተቋም ወይም ከእንስሳት መድኃኒት አምራች ወይም ጅምላ አከፋፋይ ወይም ቸርቻሪ ድርጅት በስተቀር ማንኛውም ሰው በእንስሳት ጤና ባለሙያ ትዕዛዝ የሚሰጥ የእንስሳት መድኃኒት መያዝ አይችልም፤

   4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የታካሚ እንስሳት ባለቤት በእንስሳት ጤና ባለሙያ የታዘዙ መድኃኒት ከእንስሳት መድኃኒት ቤት ገዝቶ

የሕክምና አገልግሎት ወደ ሚሰጥበት የእንስሳት ጤና ተቋም የሚወስድን አይመለከትም፤

6. በማዘዣ ወረቀት የታዘዘ መድኃኒት ስለማደል

1. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ፈቃድ በተሰጠው የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ መታደል አለበት፤
2. ማንኛውም የታካሚ እንስሳት ባለቤት መድኃኒት መግዛት ያለበት ህጋዊ ከሆነ የእንስሳት መድኃኒት ቤት ነው፤
3. በእንስሳት ጤና ባለሙያ ብቻ የሚታዘዝ መድኃኒት አገልግሎት ላይ ለመዋል ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ የሚከተሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፤

   ሀ) መድኃኒት ከማደሉ ወይም ከማሰራጨቱ ወይም ጥቅም ላይ እንዲውል ከማድረጉ በፊት የታዘዘውን የእንስሳት መድኃኒት ተገቢነት መገምገም፤

   ለ) ስለሚያድለው መድኃኒት ለታካሚ እንስሳት ባለቤት በቂ መረጃና ምክር መስጠት፤

   ሐ) የታዘዘውን መድኃኒት ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ እና ከሕክምና ማዘዣው መስፈርት ጋር የሚስማማ መሆኑን ማረጋገጥ፤

4. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የተጠቀሱትን የእንስሳት መድኃኒቶች ሊያድል የሚችል ቢሆንም ይህንን ስራ ለሌሎች የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያዎች ውክልና ሊሰጥ አይችልም፤
5. በእንስሳት ጤና ባለሙያ የሚታዘዝ መድኃኒት ከባለሙያ ትዕዛዝ ውጪ ሊወሰዱ ከሚችሉ የእንስሳት መድኃኒት ተለይተው በመደርደሪያ መቀመጥ አለበት፡፡

7. ቁጥጥር የሚደረግበት የእንስሳት መድኃኒት ስለማዘዝ

1. ቁጥጥር የሚያስፈልገው የእንስሳት መድኃኒት በአዝል 6 ላይ በተመላከተው መሰረት በጥብቅ ክትትል በልዩ ማዘዣ ወረቀት በእንስሳት ሐኪም ትዕዛዝ ብቻ መታዘዝ አለበት፤

2. ማንኛውም የእንስሳት ሐኪም በቂ ክሊኒካል ማስረጃ የሌለውን ቁጥጥር የሚደረግበትን የእንስሳት መድኃኒት ማዘዝ አይችልም፤

3. ሌሎች የእንስሳት ጤና ባለሙያዎች በእንስሳት ሐኪም ቁጥጥር ስር ካልሆነ በስተቀር በዕዝል 1 ላይ የተጠቀሱትን ቁጥጥር የሚደረግባቸው የእንስሳት መድኃኒት ማዘዝ አይችሉም፤

4. ልዩ ማዘዣ ወረቀት በዕዝል 6 ላይ የተመለከቱትን የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

   ሀ) ማዘዣ ወረቀቱ የተሰጠበት ቀን፤

   ለ) የታካሚ እንስሳት ባለቤት ሙሉ ሥም፤

   ሐ) አድራሻ፤

   መ) የመድኃኒቱ ሥም፤

   ሠ) ጥንካሬ፤

   ረ) መጠን፤

   ሰ) አጠቃቀም መመሪያዎች፤

   ሸ) የባለሙያው ሥም፤

   ቀ) አድራሻ እና፤

   በ) የምዝገባ ቁጥር፡፡

8. **በልዩ ማዘዣ የእንስሳት መድኃኒት ስለማደል**

1. ማንኛውም ቁጥጥር የሚደረግበት የእንስሳት መድኃኒት መታደል ያለበት ከእንስሳት ሐኪም በልዩ ማዘዣ ሲጠየቅ ብቻ ነው፤

2. ቁጥጥር የሚደረግበት የእንስሳት መድኃኒት በልዩ ክፍል ተቆልፎ መቀመጥ እና ቁልፉ በተፈቀደለት የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ እጅ ብቻ መቀመጥ አለበት፤

3. ከእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ በስተቀር ማንኛም ሰው ቁጥጥር የሚደረግበትን የእንስሳት መኃኒት ማደል አይችልም፤

4. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ በዕዝል 1 ላይ የተጠቀሰውን መድኃኒት የሚያድለው የአዛዡ አድራሻ በኢትዮጵያ ውስጥ መሆኑን እና የማዘዣው ትክክለኛነት ሲረጋገጥ ብቻ ነው፤

5. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ የልዩ ማዘዣ ወረቀቱ በሀሰት ወይም በህገ-ወጥ መንገድ መጻፉን ወይም መቀየሩን ወይም መሰረዙን ካወቀ ቁጥጥር የሚደረግበት የእንስሳት መድኃኒት ማደል የለበትም፤
6. ቁጥጥር የሚደረግበት የእንስሳት መድኃኒትን በፋክስ ወይም በኤሌክትሮኒክስ ማዘዣ ማደል የተከለከለ ነው፡፡

## 9. የእንስሳት መድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ሕጋዊነት

1. የማዘዣ ወረቀት ሕጋዊነት ሊረጋገጥ የሚችለው በዚህ መመሪያ ዕዝል 5 ላይ የተቀመጡ መስፈርት ከተሟሉ ብቻ ነው፤
2. ልዩ የማዘዣ ወረቀት ሕጋዊነት ሊረጋገጥ የሚችለው በዚህ መመሪያ እዝል 6 ላይ የተቀመጠውን መስፈርት ካሟላ ብቻ ነው፤
3. የተሳሳተ ማዘዣ ወረቀት መቀየር የሚችለው ያዘዘው ባለሙያ ብቻ ነው፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የተሳሳተ ማዘዣ ወረቀት ያዘዘው ባለሙያ ለሌላ የእንስሳት ጤና ባለሙያ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፤
5. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ አነስተኛ ስህተት ያለው ማዘዣ ወረቀት ተቀብሎ መድኃኒት ማደል የሚችለው፡-
   ሀ) አሳማኝና በቂ ምክንያት የቀረበ ከሆነ፤
   ለ) ጥቃቅን የአፃፃፍ ስህተት ወይም የፊደል ግድፈት ከሆነ ወይም
   ሐ) የሐኪም ማዘዣ ወረቀት በቀለም ወይም በሌላ መንገድ ያልተቀየረ ከሆነ ነው፡፡

# ክፍል ሦስት

# ያለማዘዣ ወረቀት መድኃኒትን ስለማደል

## 10. ያለማዘዣ ወረቀት ሊታደል የሚችል የእንስሳት መድኃኒት

1. ያለማዘዣ ወረቀት ሊታደል የሚችል የእንስሳት መድኃኒት በእዝል 4 እንደተዘረዘረው የሚከተሉትን መስፈርት የሚያሟላ መሆን አለበት፡-
   ሀ) አደጋ የማጋለጥ እድሉ ሰፊ ያልሆነ፤
   ለ) ተጨማሪ ምርመራ የሚያስፈልጋቸው ንጥረ ነገር ያልያዘ ከሆነ፤
   ሐ) በመርፌ መልክ የማይሰጥ፤
   መ) ከፍተኛ መርዛማነት ወይም ከባድ የጎንዮሽ ጉዳት የሌለው፤

ሠ) የተህዋስያን መላመድ የማስከተል እድሉ አነስተኛ የሆነ፤

ረ) ያለአግባብ ጥቅም ላይ ሲውል የከፋ የጤና እክል የማያስከትል፤

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 1 ስር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ያለማዘዣ ወረቀት ሊታደል የሚችል የእንስሳት መድኃኒት በእንስሳት ጤና ባለሙያ ወይም በእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ ችግር እንደሌለው ካልተረጋገጠ በስተቀር ከማናቸውም ሌሎች የእንስሳት መድኃኒት ጋር አብሮ መሰጠት የለበትም፡፡

## 11. የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ ግዴታዎች

ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ፡-

1. ከታካሚ እንስሳት ባለቤት ስለበሽታው ዓይነት፣ ምልክት እና የህክምና ቅድመ ታሪክ በቂ መረጃ በመሰብሰብ የችግሩን ሁኔታ ወይም አስከፊነት ሲያረጋግጥ ብቻ መድኃኒቱን በመምረጥ ማደል አለበት፤
2. በሚከተሉት ሁኔታዎች ላይ መሠረት አድርጎ ለታካሚ እንስሳት ባለቤት በቂ የምክር አገልግሎት መስጠት አለበት፤

   ሀ) የመድኃኒቱን ስም፣ ዓይነት፣የአሰጣጥ ዘዴና መጠን፤

   ለ) እንስሳው ከበሽታው መፈወስ የሚጀምርበትን ጊዜ፤

   ሐ) የህክምናውን ጥቅም፤

   መ) የመድኃኒቱን የጎንዮሽ ጉዳት፤

   ሠ) እንስሳው ከበሽታው  ካልተፈወሰ ምን ማድረግ እንዳለበት፤

   ረ) የመድኃኒቱን አቀማመጥ እና አያያዝ፤

   ሰ) መድኃኒቱ ጎጂ ባህሪያት የሚያስከትል ከሆነ ወዲያውኑ ሪፖርት እንዲያደርጉ፤

   ሸ) መድኃኒቱ በምን ያህል የቀን ልዩነት ለምን ያህል ቀን እንደሚሰጥ፤

   ቀ) የመድኃኒት ቅሪት ከእንስሳው አካል የሚወገድበት ጊዜ፤
3. አማራጭ ያለማዘዣ የሚታደሉ የእንስሳት መድኃኒት ለታካሚ እንስሳት ባለቤት ምክር መስጠት አለበት፤
4. ያለማዘዣ ወረቀት የሚታደሉ የእንስሳት መድኃኒት በአምራቹ የመጀመሪያ ማሸጊያ ብቻ ማደል ወይም መሸጥ አለበት፤
5. ያለማዘዣ ወረቀት የሚታደሉ የእንስሳት መድኃኒት እንደገና አሽጎ ማደል የለበትም፤
6. ለተጠርጣሪ በሽታ አማራጭ ያለማዘዣ ሊታደል የሚችል መድኃኒት ከሌለ ከእንስሳት ጤና ባለሙያ እርዳታ እንዲጠይቁ ለታካሚ እንስሳት ባለቤት ምክር መስጠት አለበት፤

7. ደህንነቱና ውጤታማነቱ የተረጋገጠ መድኃኒት ለታካሚ እንስሳት ባለቤት ማደል አለበት፤

8. መድኃኒት ለታካሚ እንስሳት ባለቤት በሚያድልበት ጊዜ የመድኃኒቱን ንግድ ስም መጠቀም የለበትም፤

9. ማንኛውንም የእንስሳት መድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ወይም ሰነድ ቁልፍ ባለው ቁምሳጥን መያዝ አለበት፤

10. የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው የእንስሳት መድኃኒቶች ማሸጊያ ወይም መያዣ ላይ በስህተት ለተጠቃሚ እንዳይታደሉ ወይም እንዳይሸጡ "**ጊዜው ያለፈበት**" የሚል ምልክት ማድረግ አለበት፡፡

## 12. የታካሚ እንስሳት ባለቤት ግዴታዎች እና ኃላፊነቶች

ማንኛውም የታካሚ እንስሳት ባለቤት፡-

1. ያለማዘዣ ወረቀት የሚታደል የእንስሳት መድኃኒት ለመጠቀም የሚከተለውን ተግባራት ማከናወን ይኖርበታል፡-
   ሀ) የበሽታውን ምልክቶች በሚገባ በመገንዘብ ለእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ መግለፅ፤
   ለ) የህክምናውን ዓላማ እና ጥቅም ማወቅ፤
   ሐ) የታካሚውን እንስሳት የህክምና ቅድመ ታሪክ ማወቅ፤
   መ) የእንስሳት ጤና ባለሙያ ወይም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ ምክር በትክክል መተግበር፤
   ሠ) መድኃኒቱን ከታዘዘለት ታካሚ እንስሳት ውጪ አለመጠቀም፤
   ረ) መድኃኒቱን ለሌላ ሦስተኛ ወገን አሳልፎ አለመስጠት፤
   ሰ) መድኃኒቱን ህፃናት በማይደርሱበት ቦታ ወይም ይዘቱን ሊያዛባ ከሚችል ነገሮች አርቆ ማስቀመጥ፤
2. ያለማዘዣ ወረቀት ሊታደል የሚችል የእንስሳት መድኃኒት ለታካሚ እንስሳት ከመስጠቱ በፊት የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያውን ትዕዛዝ በጥንቃቄ መረዳትና መተግበር አለበት፤
3. በአንድ ጊዜ ከአንድ ዓይነት በላይ ያለማዘዣ የሚታደል የእንስሳት መድኃኒት ለታካሚ እንስሳት መስጠት የለበትም፤

4. ያለማዘዣ የሚታደል የእንስሳት መድኃኒት በተመለከተ ማንኛውም አጠራጣሪ ነገር ካጋጠመ መድኃኒቱን ከሸጠለት የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ ምክር ማግኘት አለበት፤
5. የእንስሳት መድኃኒት በታካሚ እንስሳት ላይ የጎጂ ባህሪ ምልክት የሚያሳይ ከሆነ ለእንስሳት ጤና ባለሙያ ወይም ለእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ ማሳወቅ አለበት፤
6. ለተጠርጣሪ በሽታ አማራጭ ሕክምናን ከመምረጡ በፊት የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያን ምክር መጠየቅ አለበት፤
7. የእንስሳት መድኃኒት ህጋዊ ከሆኑ የእንስሳት መድኃኒት ቤት ብቻ የመግዛት ግዴታ አለበት፤
8. ያለማዘዣ ሊታደል የሚችል የእንስሳት መድኃኒት ያለእንስሳት ጤና ባለሙያ ወይም ያለእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ የምክር አገልግሎት በተከታታይ ለረጅም ጊዜ መጠቀም የለበትም።

## 13. ያለማዘዣ የሚታደል የእንስሳት መድኃኒት ገላጭ ጽሁፍ

1. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ ያለማዘዣ የሚታደል የእንስሳት መድኃኒት ከማደሉ በፊት ገላጭ ጽሁፉ የሚከተለውን መረጃ የያዘ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤
   ሀ) የእንስሳት መድኃኒቱን ንጥረ ነገርና መጠናቸው፤
   ለ) የእንስሳት መድኃኒቱ ለምን ዓላማ እንደሚውል፤
   ሐ) የእንስሳት መድኃኒቱን አጠቃቀም ዘዴ፤
   መ) በማንኛው ሁኔታ መድኃኒቱ ጥቅም ላይ መዋል የማይኖርበትን ሁኔታዎች የሚገልጹ ማስጠንቀቂያዎች፤
   ሠ) ከእንስሳት ጤና ባለሙያ ወይም ከእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ ጋር መማከር ተገቢ የሚሆንበትን ጊዜ፤
   ረ) የጎንዮሽ ጉዳቶች እና ችግሩን ለማስቀረት መሰራት የሚገባውን ስራ፤
   ሰ) የመድኃኒቱ አሰጣጥ መመሪያዎች መቼ፣ እንዴት እና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚሰጥ፤
   ሸ) የእንስሳው ዝርያ፤
   በ) መድኃኒቱ ምን ዓይነት በሽታ ለማከም እንደሚያገለግል፤
   ተ) የመድኃኒት ቅሪት ከእንስሳው አካል የሚወገድበት ጊዜ፤
   ቸ) መድኃኒቱ **ለእንስሳት ህክምና ብቻ** እንደሚሰጥ መግለጽ፤

2. የታካሚ እንስሳት ባለቤት ያለማዘዣ የሚታደል የእንስሳት መድኃኒት ገላጭ ፅሁፍ አንብቦ እና ስለ መድኃኒቱ ጥያቄ ካለው የእንስሳት ጤና ባለሙያን ወይም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያን ማማከር አለበት፡፡

14. **መዝገብ አያያዝ**

1. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ የመድኃኒት ሽያጭ ሲያከናውን መድኃኒቱ የታዘዘበትን ቀን፣ የታካሚ እንስሳት ባለቤት ስምና አድራሻ፣ የእንስሳው ስም ወይም መለያ ቁጥር፣ ዝርያና ፆታ፣ የመድኃኒት ስም፣ ጥንካሬና መጠን፣ የምርመራ ውጤት፣ መድኃኒቱን ያዘዘው የእንስሳት ጤና ባለሙያ ስም እና በሽያጩ ውስጥ የተሳተፉትን የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያዎች ስም መመዝገብ አለበት፤
2. ማንኛውም የእንስሳት ጤና ባለለሙያ የተገዛን ወይም በእርዳታ የተገኘን የእንስሳት መድኃኒት በሞዴል 19 ለእንስሳት መድኃኒት ቤት ገቢ መሆኑን ማረጋገጠ አለበት፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ስር የተገለጸው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ በማዘዣ ወረቀቱ መሠረት ለታካሚ እንስሳት ባለቤት የሚያድለውን መድኃኒት ከእንስሳት መድኃኒት ቤት በሞዴል 22 ወጪ ማድረግ አለበት፤
4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የእንስሳት መድኃኒቶች መዝገብ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

   ሀ) የግዥ ወይም ሽያጭ ደረሰኝ መዛግብት፤

   ለ) የመድኃኒት አሰጣጥና የዕደላ ማስታወሻዎች፤

   ሐ) የጠፉ ወይም የተሰረቁ መድኃኒቶች ሪፖርት፤

   መ) የመድኃኒት ቆጠራ፤

   ሠ) የሐኪም ማዘዣ ሰነዶች፤

   ረ) የኦዲት ግኝቶች፤

   ሰ) የተወገዱ ወይም የተመለሱ መድኃኒቶች፤

   ሸ) የተላለፉ መድኃኒቶች ዝርዝር፤
5. የመጀመሪያ ማሸጊያቸው የተከፈተ ወይም ሙሉ ለሙሉ አገልግሎት ላይ ያልዋሉ የእንስሳት መድኃኒቶች አገልግሎት ላይ እስከሚውሉበት ወይም የመጠቀሚያ ጊዜው

እስካላለፈ ድረስ ከሌላ መድኃኒት ወይም በተለያየ ምክንያት እንዲወገዱ ተብለው ከተቀመጡ ወይም ከተከማቸ መድኃኒት ተለይተው በልዩ ቦታ መቀመጥ አለበት፤

6. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት የታደለበት የእንስሳት መድኃኒት ማዘዣ ወረቀት ቢያንስ ለሁለት ዓመት በእንስሳት መድኃኒት ቤት መቀመጥ አለበት፤
7. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ ስለተገዛውና ስለታደለው የእንስሳት መድኃኒት መረጃ በመሰብሰብ በዓመቱ መጨረሻ አግባብ ላለው አካል ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 15. አስተዳደራዊ እርምጃ

1. ማንኛውም የእንስሳት መድኃኒት ባለሙያ በአንቀጽ 11 ስር የተደነገገውን ድንጋጌ ለመጀመሪያ ጊዜ በመጣስ መድኃኒት ካደለ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ይደረጋል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በአንቀጽ 11 የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች ከሁለት ጊዜ በላይ በተደጋጋሚ የሚጥስ ከሆነ የሙያ ፈቃዱና የብቃት ማረጋገጫው ለአንድ ዓመት እንዲታገድ ይደረጋል፡፡

### 16. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም የአሰራር ልምድ በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

### 17. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ጳጉሜ፣2016

አምባሳደር ድሪባ ኩማ

የግብርና ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር

### እዝል 1፡ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የእንስሳት መድኃኒቶች

| **Schedule II** | Dosage form | **Schedule III** | **Dosage form** | **Schedule IV** | **Dosage form** |
|---|---|---|---|---|---|
| Ketamine hydrochloride | Injection | Secobarbital | Injection | Diazepam | Injection |
| Methadone | Injection, Oral suspension Tablet | Buprenorphine hydrochloride | Injection | Serum gonadotropin | Powder for injection |
| Morphine hydrochloride | Injection | Thiopentone sodium | Powder for injection | Clenbuteral hydrochloride | Oral Syrup |
| Pethidine hydrochloride | Injection | | | Testosterone | Injection |
| Quinalbarbitone sodium | Injection | | | | |
| Pentobarbitone sodium | Injection | | | | |
| Acepromazine maleate | Injection | | | | |

### እዝል 2፡ በእንስሳት ሐኪም ብቻ የሚታዘዙ መድኃኒቶች

| **Anesthetic Drugs** | |
|---|---|
| **Name** | **Dosage Form** |
| Alfaxalone | Injection |
| Atipamezole hydrochloride | Injection |
| Atropine sulfate | Injection |
| Ether | Inhalation |
| Halothane | Inhalation |
| Isoflurane | Inhalation |
| Mapivacaine | Injection |
| Methohexitone sodium | Powder for injection |
| Propofol | Injection |
| Sevoflurane | Inhalation |
| **Hormones** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Buserelin | Injection solution |
| Chorionic Gonadotropin + Estradiole Benzoate | Injection |
| Cloprostenol sodium | Injection |
| Dinoprost | Injection |
| Equine chorionic gonadotropin | Injection |
| Gonadotropin Releasing Hormone | Injection |
| Gonadorelin | Injection |
| Luprostiol | Injection |

| | |
|---|---|
| Megestrol acetate | Tablet |
| Methyl propionate | Injection |
| Estradiol benzoate | Injection |
| Oxytocin | Injection |
| Progesterone | Injection, Vaginal delivery |
| **Neuroleptics/Sedatives** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Detomedine hydrochloride | Injection |
| Dexmedetomidine | Injection |
| Medetomidine hydrochloride | Injection |
| Romifidine hydrochloride | Injection |
| Xylazine | Injection |
| **Analgesics/Antipyretics** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Antonidine | Injection |
| Butorphanol | Injection |
| Detomidine hydrochloride | Injection, Oral gel |
| Hyoscine Butyl bromide | Solution for Injection |
| Medetomidine | Injection |
| Metamizole sodium | Injection |

## እዝል 3: በእንስሳት ጤና ባለሙያ የሚታዘዙ መድኃኒቶች

| **Antibacterial** | |
|---|---|
| **Pencillins** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Benzathine pencillin G + Procaine pencillin G | Ointment, Injection, Powder for injection |
| Procaine benzyl penicillin | I/M/Suspension, Injection |
| Amoxicillin and its combinations | Capsule, Injection, Oral suspension, Oral powder, Powder for injection, Tablet and any other dosage form |
| Ampicillin and its combinations | Capsule, Injection, Oral powder, Tablet and other dosage form |
| Cloxacillin | Eye ointment, I/M/Suspension |
| Penethamate | Powder for injection, |
| Phenoxymethyl pencillin | Oral powder |
| Any Combinations Pencillin groups | In any dosage form |

| **Aminoglycosides** | |
|---|---|
| **Name** | **Dosage Form** |
| Streptomycin sulfate | Injection, Oral solution |
| Dihydrostreptomycin + Streptomycin | Injection, |
| Gentamicin Sulfate | Injection, Oral Powder, I/M suspension, Eye |
| Kanamycin | Injection, Oral powder, Spray |
| Spectinomycin | Injection, Oral solution |
| Any combinations of Aminoglycoside groups | In any dosage form |
| **Macrolides** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Erythromycin | I/M/Suspension, Oral powder |
| Tylosin | Injection, Oral powder/Granule, Tablet |
| Gamithromycin | Solution for injection |
| Spiramycin | Injection |
| Tildipirosin | Solution for injection |
| Tilmicosin | Oral granules, Oral solution, Solution for injection |
| Tulathromycin | Solution for injection |
| Tylvalosin | Oral Granule |
| Any combinations of Macrolides groups | In any dosage form |
| **Tetracyclines** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Chlortetracycline and its combinations | Bolus, Eye ointment, Intrauterine bolus, Oral solution, Powder, Spray, any other dosage form |
| Doxycycline and its combinations | Capsule, Injection, Oral powder, Tablet, Oral solution, any other dosage form |
| Oxytetracycline and its combinations | Injection, Aerosol Spray, I/M/Suspension, I/U/Bolus, I/U/Solution, Oral powder, Pessary, Tablet, any other dosage form |
| Any combinations of Tetracycline groups | In any dosage form |
| **Sulphonamides** | |
| **Name** | **Dosage** |
| Sulphonamide drugs and its combinations | In any dosage form. |
| **Cephalosporin** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Cefovecin | Powder for injection |
| Cephalexin and its combinations | Tablet, any other dosage form |
| Cephapirin | Powder for injection, I/M/Suspension |
| Cephalonium | Intrauterine suspension, I/M/Suspension |
| **Quinolones** | |

| Name | Dosage |
|---|---|
| Ciprofloxacin | Injection, Oral powder, Oral suspension |
| Enrofloxacin | Injection, Tablet, Oral powder, Oral solution, I/M suspension |
| Flumequin | Injection, Oral powder, Oral suspension |
| Marbofloxacin | Injection, Tablet, Powder for injection |
| Norfloxacin and its combinations | Injection, Oral powder, Oral solution, any other dosage form |
| Pefloxacin | Oral powder |
| Pradofloxacin | Tablet, Oral suspension |
| **Lincosemides** | |
| **Name** | **Dosage** |
| Lincomycin Hydrochloride and its combination | Injection, Oral powder, Oral solution and any other dosage form |
| Pirlimycin | I/M/ infusion |
| **Other antibacterials** | |
| Florfenicol and its combinations | Injection, Oral solution, Oral granules,any other dosage form |
| Fusidic acid | |
| Salinomycin | Oral powder |
| Tiamulin | Solution for injection, Oral solution, Oral granules |
| **Antifungal Drugs** | |
| **Name** | **Dosage form** |
| Amphotericin-B | Injection solution, Powder for injection, Topical, |
| Chlorhexidine digluconate+ Miconazole nitrate | Shampoo |
| Clotrimazole | Cream/Ointment |
| Copper sulfate | Oral powder |
| Enilconazole | Cutaneous emulsion |
| Fluconazole | Injection, Oral suspension, Tablet |
| Itraconazol | Oral solution, Capsule |
| Ketoconazole | Tablet, Oral suspension |
| Natamycin | Topical ointement |
| Nystatin and its combinations | Oral powder, any other dosage form |
| Zinc sulphate | Oral powder |
| **Antitrypanosomal Drugs** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Amicarbalide | Solution for injection |
| Diaceturate and its combinations | Solution for injection, Powder/ Granule for injection and in any other dosage form |

| | |
|---|---|
| Imidocarb | Solution for injection |
| Isomethamidium chloride | Powder for injection, Granule for injection |
| Melarsomine | Injection Solution, Powder for injection |
| Pentamidine | Powder for injection |
| **Anthelmentic** | |
| **Benzimidiazoles** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Albendazole | Oral Suspension |
| Febantel | Oral Suspension |
| Febendazole | Oral Suspension |
| Mebendazole | Oral suspension |
| Oxybendazole | Oral suspension |
| Oxyclozanide | Oral suspension |
| Oxyfendazole | Oral suspension |
| Any combinations of Benzimidazoles | Oral Suspensions |
| **Microcyclic lactones** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Abamectin | Injection |
| Ivermectin | Injection, oral solution |
| Any Combinations of Microcyclic Lactones | Oral Suspensions |
| **Imidazothiazoles** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Levamisole | Injection, oral suspension |
| Tetramisole | Injection |
| Any Combinations Imidazothiazole | Oral Suspensions |
| **Salicylanilides** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Closantel | Injection, oral suspension |
| Rafoxanide | Injection |
| **Others** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Praziquantel | Injection, Spot on |

| Acaricides & Insecticides | |
|---|---|
| **Name** | **Dosage Form** |
| Afoxolaner | Tablet |
| Amitraz | Liquid, Powder /Granule, Pour on |
| α- Cypermethrin | Pour-on solution |
| Carbaryl | Collar |
| Chlorfenvinphos and its combinations | Liquid and in any other dosage form |
| Cyhalothrin | Emulsifiable liquid, Pour-on solution |
| Cypermethrin | Emulsifiable Liquid, Powder, Pour-on solution, Collar |
| Cyromazine | Pour-on solution |
| Deltamethrin | Emulsifiable Liquid, Pour-on solution, Collar |
| Diazinon and is combinations | Liquid, any dosage form |
| Dichlorovos and its combinations | Liquid, any dosage form |
| Dicyclanil | Pour-on suspension |
| Fenthion | Liquid |
| Fenvalerate | Emulsifiable Liquid |
| Fipronil and its combinations | Spot-on, Spray, any other dosage form |
| Flumethrin and its combinations | Emulsifiable Liquid, any other dosage form |
| Fluralaner and its combinations | Oral solution, Tablet, Spot-on solution, any other dosage form |
| Imidacloprid and its combinations | Spot-on solution, any other dosage form |
| Indoxacarb and its combinations | Spot –on solution, any other combinations |
| Lotilaner | Tablet |
| Permethrin | Emulsifiable liquid, Dusting powder, Pour-on solution, Shampoo, Collar |
| Phosmet | Liquid |
| Porpoxur | Spray, Collar |
| Sarolaner and its combinations | Tablet any other combinations |
| Selamectin | Spot –on solution |
| **Steroids** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Betamethasone | Tablet, Injection |
| Dexamethasone | Tablet, Injection |

| | |
|---|---|
| Hydrocortisone | Tablet |
| Methylprednisolone | Tablet, Injection |
| Prednisolone acetate | Tablet, Injection, Oral powder, Syrup |
| **Cardiovascular drugs** | |
| **Diuretics** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Chlorthiazide | Tablet |
| Furosemide | Injection, Tablet, Syrup |
| Hydrochlorothiazide | Tablet |
| Mannitol | Injection |
| Methenamine | Powder |
| **Laxatives** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Magnesium sulfate (Epsom salt) | Injection |
| **Antiemetic** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Maropitant citrate | Injection |
| Metoclopramide | Injection |
| **NSAIDs** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Acetyl salicylic acid | Injection |
| Cimicoxib | Tablet |
| Cyclosporine A | Capsule, Eye drop, Oral solution |
| Diclophenac sodium | Injection |
| Firocoxib | Injection, Oral paste, Tablet |
| Flunixin Meglumine | Injection, pour-on, oral paste |
| Ketoprofen | Injection, Oral solution, Tablet |
| Meloxicam | Granule, Injection, Oral paste, Oral suspension, |
| Pentosan polysulphate sodium | Injection |
| Polysulphated glycosaminoglycan | Injection |
| Tolfenamic acid | Injection, Oral paste, Tablet |
| **Local Anaesthetics** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Lidocaine hydrochloride | Injection, oral spray |

| | |
|---|---|
| Lidocaine + Adrenaline | Injection |
| Lidocaine hydrochloride + Noradrenaline | Injection |
| Lidocaine hydrochloride + Epinepherine acid tartrate | Injection |
| Mepivacaine | Injection |
| Procaine hydrochloride + Epinephrine acid tartrate | Injection |
| **Anticoagulants** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Heparin sodium | Injection |
| Vitamin K | Injection |
| Warfarin sodium | Tablet |
| **Fluids and Electrolytes** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Aluminium Chloride and its combinations | Oral Powder |
| Bismuth Salysilate and its combinations | Oral Suspension |
| Calcium Borogluconate and its combinations | Injectable solution, any dosage form |
| Calcium Gluconate and is combinations | Injection, any dosage form |
| Dextrose and its combinations | IV infusion, any other dosage form |
| Glucose monohydrate and its combinations | Injection, Powder, any other dosage form |
| Iron Dextrose + Vit B12 | Injection |
| Propionic acid and its combinations | Powder, any other dosage form |
| Sodium bicarbonate and its combinations | Powder, any other dosage form |
| **Vitamins, Minerals, Amino acids, Fatty acid** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Bismuth subnitrate | I/M/Suspension |
| Copper and its compounds | Paste, any other dosage form |
| Cyanocobalamin | Injection |
| Glucose Anhydrous | Injection |
| Iron | Injection |
| Magnesium sulfate | Injection |
| Selenium and its combinations | I/R/device, any other dosage form |

| | |
|---|---|
| Toldimphos sodium | Injection |
| Zinc oxide | Premix |
| **Drugs Used for Poisoning** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Activated Carbon + Kaolin | Granules, Oral suspension |
| Copper oxide | Bolus (hard capsule) |
| Epinephrine | Injection |
| Nalorphine HCL | Injection |
| Yohimbine HCL | Injection |
| **Anthelmentic** | |
| **Name** | **Dosage form** |
| Doramectin | Injection, Pour –on solution |
| Eprinomectin | Injection, Pour-on solution |
| Milbemycin Oxide | Tablet |
| Monepantel | Oral solution |
| Moxidectin | Injection, Oral gel, Oral solution, Pour-on, Tablet |
| Nitroscanate | Tablet |
| Nitroxynil | Injection |
| Pyrantel embonate | Oral paste |
| **Miscellaneous** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Benzyl Alcohol | Liquid |
| Bromhexine Hydrochloride | Oral powder |
| Clodronic Acid | Injection |
| Denaverine | Solution for Injection |
| Doxapram | Solution for Injection |
| Propylene Glycol + Cobalt Sulfate | Injection |
| Sodium hyaluronate | Injection |
| Sodium hydroxide | Cutaneous Paste |
| Parasitamol | Tablet |
| Strychnine | Oral Powder |
| **Veterinary Vaccines** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| All Viral, Bacterial, Protozoal and Fungal Vaccines listed in National Veterinary Drug list. | All dosage Form |
| **Antiseptics and Disinfectants** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| All types Antiseptics and Disinfectants Lited in National Veterinary Drug list. | All dosage form |

## እዝል4፡- ያለማዘዣ ወረቀት ሊታደሉ የሚችሉ የእንስሳት መድኃኒቶች

| **ANTHELMENTICS** | |
|---|---|
| **Benzimidazoles** | |
| **Name** | **Dosage form** |
| Albendazole | Bolus, Oral powder, Paste |
| Albendazole combinatios | Bolus |
| Febantel | Paste |
| Febantel combination | Tablet |
| Fenbendazole | Bolus, Granule/powder, Paste |
| Flubendazole | Oral powder |
| Mebendazole | Oral Granule/Powder, Paste , Tablet |
| Oxybendazole | Bolus , Oral powder |
| Oxyfendazole | Bolus |
| Thiabendazole | Eye/ear drop |
| **Microcyclic Lactones** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Abamectin | Capsule , Oral powder, Oral solution<br>Paste ,Pour –on, Tablet |
| Ivermectin | Capsule, Oral powder , Oral solution,<br>Paste /Gel, Pour-on, Tablet /bolus |
| Ivermectin combinations | Bolus |
| **Imidazothiazoles** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Levamisole | Bolus, Oral powder, Pour-on |
| Levamisole combinations | Bolus |
| Tetramisole | Bolus , Oral powder |
| Tetramisole combinations | Bolus |
| **Salicylanilides** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Niclosamide | Bolus , Oral powder, Paste |

| | |
|---|---|
| Niclosamide combinations | Bolus |
| Oxyclozanide | Bolus |
| Oxyclozanide combinations | Bolus |
| **Substituted Phenols and Others** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Piperazine citrate | Tablet |
| Praziquantel | Tablet or Bolus |
| Praziquantel combinations | Tablet or bolus |
| Pyrantel pamoate | Paste, Tablet |
| **ANTIPROTOZOALS** | |
| **Anticoccidials** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Amprolium hydrochloride | Oral powder, Oral solution |
| Amprolium hydrochloride+ Furafolidine + Vitamin K + Vitamin A | Oral powder |
| Amprolium hydrochloride+ sulfaquinoxaline | Oral powder |
| Amprolium hydrochloride + sulfaquinoxaline + Vitamin K | Oral powder |
| Amprolium hydrochloride + vitamin K | Oral powder |
| Halofuginone | Oral solution |
| Lasalocid A sodium | Oral powder |
| Monensin | Oral powder |
| Robendine HCL | Oral powder |
| Toltrazuril | Oral Solution |
| **GASTROINTESTINAL DRUGS** | |
| **Anti-Diarrheal drugs** | |
| **Name** | **Dosage** |
| Kaolin + pectin | Oral suspension |
| **Bloat Remedy** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Dimeticone | Oral suspension |
| Docusate | Oral suspension |

| | |
|---|---|
| Poloxalene | Oral suspension |
| Simethicone | Oral emulsion |
| **Emollient/Lubricant/Hyperosmotic/Stimulant Laxatives** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Bisacodyl | Tablet |
| Epson salt | Powder |
| Ispaghula HUSK | Oral powder , Oral granule |
| Magnesium hydroxide mixture | Cream |
| Paraffin | Oral paste |
| **Antiulcer and Antiemetic** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Cimetidine | Tablet |
| Maropitant citrate | Tablet |
| Metoclopramide | Oral solution |
| Omeprazole | Oral paste |
| **Analgesics/Antipyretics** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Acetyl Salicylic Acid | Bolus, Tablet/capsule |
| Paracetamol | Oral solution, Tablet |
| **Antitussive/Expectorant/Mucolytic** | |
| **Name** | **Dosage Form** |
| Bromhexine hydrochloride | Oral powder |
| **MISALLENOUS** | |
| Iodine Tincture | |
| NaCl | |
| Zinc Oxide Ointment | |
| KI | |
| Alcohol | |

## እዝል 5፡ የእንስሳት መድኃኒት ማዘዣ ወረቀት

Date________________________

Ser.No, ------------------------------

Case No.____________

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

**[Name of the Ministry/Regional Bureau/Private clinic/NGO]**

**Veterinary Prescription Paper**

Date________________________

Ser.No, ------------------------------

Case No.____________
Institution________________________________________
Address: Region___________Zone________Woreda________Town_________Tel__________
Owner's Name_____________________________________
Address: Region__________Town__________Woreda_________Keble_______locality______
Species of animal(s) __________Age___________Sex__________
Body weight___________Identity of animal______________
Diagnosis _____________________________________

| Treatment given (name, strength, route of administration, dosage form, dosage and quantity of drug) | Price of Each item | |
|---|---|---|
| | Birr | Cent |
| | | |

Refill ________________________________________ Withdrawal period_________________

Prescriber's
Name_____________________________
Qualification________________________
Registration No.____________________
Signature___________________________
Date________________________________
* Seal over leaf

Dispenser's
___________________________
____________________________
___________________________
___________________________
___________________________

**N.B.**

1. The Prescription should bear the seal of the animal health Institution
2. Prescribers should
    - write the prescription correctly and legibly
    - treat prescription paper as personal cheque book
    - be receptive to calls from dispenser who is trying to verify prescription
    - write refill order as per the list of refillable drugs

3. Dispensers should
    - Check if the prescription is legible and neat in appearance
    - review prescription carefully and verify with prescriber if it is incorrectly prescribed
    - Keep filled and blank (when applicable) prescription paper in the pharmacy section
    - Register and keep filled prescription for at least two years
    - Do not dispense copied and in deleted prescription.
    - Dispense single prescription for one time only unless stated as refill for refillable drugs

## እዝል 6፡ ልዩ የእንስሳት መድኃኒት ማዘዣ ወረቀት

**Name of the Institution**

**Address————**

**Controlled Drug Rx**

S. No————————————

Date: ————————————

Owner’s Name: ————————      Species of Animals: ——————

Address: ——————————      Age: —— Sex: ——— Bwt: ———

Identity of Animals: ————————

| Rx (name, strength, route of administration, dosage form, dosage) | Quantity Dispensed |
|---|---|
| | |

Prescribed By: ———————      Dispensed By: ———————

Signature——————————      signature——————————

Date————————————      Date——————————

Stamp of the Institute      Pharmacy Name, Address and Stamp